‘ዓምደ ሃይማኖት’ ፥ የቃሉ ትርጓሜ በአጭሩ በአማርኛችን ሲነገር “የእምነት ምሰሶ” ማለት ነው ። ምሰሶ ቤትን እንዳይፈርስ ጣሪያና ግድግዳውን ደግፎ አጽንቶ እንደሚኖር ፥ ሃይማኖትም የምዕመናንን ልቡና ከጥርጥር ፥ ከክህደት ጠብቆ በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ አጽንቶ በደግ ምግባር ደግፎ ከመንፈሳዊ ውድቀት ለመጠበቅ ስለሚረዳቸው በምሰሶ ተመስሏል ። መጻሕፍትን በየክፍላቸው መጥኖ ለመመልከት የዐምድ መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል ። በዚሁ ዓይነት ተምሳሌት የሃይማኖትን ትምህርት ነገረ መለኮትን ማለትም ቲዎሎጂን ( Th:ology ) ለማጥናት ይቻል ዘንድ ዐምደ ሃይማኖት በሚል ርዕስ አቅርበናል ።

# መጽሐፍ ቅዱስ 81 ወይስ 66 ?

ከነ መድኅን አባተ

በዚህ ዐቢይ ርእስ ሥር በተከታታይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ጠቅላላ ነገረ ሃይማኖት ለማቅረብ ታስቧል ። ዓላማውም ክርስቲያናዊው ሕብረተሰብ የእምነቱን ምንጭና ትበሃሉን ከለማወቅ የተነሣ መንፈሳዊ ሕይወቱ እንዳይጕሳቆል ትምህርት ለመስጠት ነው ። የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምሁራን የሚሳተፉበት መሆኑን በመገንዘብ ለጊዜው ጥልቅና ምጡቅ የሆነውን ‘ትምህርተ መለኮት’ ለሊቃውንቱ ትተን ቀለል ባለ አባባል ለማንኛውም ምዕመን እንዲረዳው በማሰብ ለማቅረብ እንሞክራለን ።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታችን በምድ የቆመው ወይም የተመሠረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው ። በተለይ በዚህ ጽሑፍ ቤተክርስቲያኒቱ ስለተቀበለቻቸው ስለ 81 ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥርና ከእነዚህ ውስጥ በሌሎች ዘንድ ከቁጥር የወጡትን ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን ያገኦደሏቸውን ለምን እንደምንቀበላቸው እንዘረዝራለን ። በቅድሚያ ከልደተ ክርስቶስ በፊትና በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገቡና ስለኢትዮጵያውያን ሃይማኖት ጥንታዊነት መግለጹ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል ። በጽሑፋችን ታሪካዊ አመጣጡን በመጠኑ በአጠቃላይ መልኩ እንዳስሰዋለን ።

## ሃይማኖት በኢትዮጵያ

ከጥፋት ውሃ በኋላ ከኖኅ ልጅ ከካም የተወለደው ኩሽ ከልጆቹ ከሳባና ከአፌስ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የአያቴን የኖኅን ሃይማኖት በአንድ አምላክ ማመንን ( Monotheism ) ይዞ ገብቷል ። ኢትዮጵያ በኖኅ ዘመን በሕገ ልቡና በእግዚአብሔር የምታመልክ ሀገር በመሆኗ በጥንታዊ የግብጻውያን ቋንቋ ሳይቀር ጴንጥ ቶ ኔቶር ተብላ ትጠራ ነበር ። ጴንጥ ዘፍጥ 10 ቁ. 6 ፉጥ ከሚለው ስም ጋር ሲመሳሰል ቶ ኔቶር ማለት ግን ሀገረ እግዚአብሔር ማለት መሆኑ ታውቋል ።

ሙሴ ብሉይ ኪዳንን ሲጽፍ ሀገሪቱን “የኩሽ ምድር” ብሎ መጥራቱ በዕብራይስጥ ቋንቋ ሳይሆን የግብፅን ቋንቋ ስለሚያውቅ በጥንታዊው ልሣነ ግብፅ ነበር ። የኩሽ ሁለተኛ ስሙ ኢትዮጲስ ይባላል ። በኢትዮጲስ ኢትዮጵያ ተብላለች ። በሳባ “የሳባ ምድር” በአቢስ “አቢሲኒያ” ትባላለች ። ዐረቦች “ሐበሽ” “ውጥንቅጥ” “ድብልቅልቅ” ለማለት ቢቃጡም ታሪካዊ ምንጭ የለውም ። በሕገ ልቡና በዘመነ አበው ሀገረ እግዚአብሔር መሆኗ ከታወቀ ዘንድ በዘመነ ነገሥት ኃላፊያትና መጻእያት የተገለጸለት ታላቁ መዘምር ነቢዩ ዳዊት ስለ ኢትዮጵያ ሃይማኖት “አማላጆች ከግብጽ ይመጣሉ ። ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች” (መዝ. 67 ቁ. 31) ሲል ተናግሯል ።

ይህም ትንቢታዊ አነጋገር በዳዊት ልጅ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ሳባ በኢትዮጵያ ነግሣ ሳለ ከእስራኤል ታቦተ ጽዮን ፥ ብሉይ ኪዳን ፥ ሥርዓተ ኦሪት በመጣ ጊዜ መፈጸም ጀምሮ ጌታ ከድንግል ማርያም ሲወለድ ኢትዮጵያውያን ሊሰግዱለት አምሃ (ገጸ በረከት) ይዘው ኢየሩሳሌም ሄደው በገበሩለት ጊዜ በኢትዮጵያ ባዚን በነገሰበት ዘመን ተፈጽሟል ። (መዝ. 71 ቁ. 9—11)

ከዚህ ላይ ዓረብን ማንሳቱ በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ግዛት እንደ ዛሬ ጠባብ ሳይሆን ዓረብን ጭምር የሚያጠቃልል ስለነበረ ነው ። ሶፎንያስ የተባለው ነቢይም ስለ ኢትዮጵያውያን ቁርባን ተወዳጅነት ስለ ሃይማኖታቸው ደገኝነት በትንቢቱ ገልጾታል ። (ሰፎ 3 ቁ 10) ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ34 ዓ.ም. በህንደኬ ጃንደረባ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነግረናል ። ይህ ሰው በኦሪታዊ እምነቱ ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሳለ በግዕዝ የተጻፈውን የኢሳይያስን ትንቢት ሲያነብ በተለይም ምዕ 53ን ሲደግም በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሐዋርያው ፊልጶስ እንዲተረጉምለት ተደርጎ በፈቃዱ የክርስትናን ሃይማኖት ተቀብሎ ተጠምቆ ለኢትዮጵያውያን የክርስትናን ዜና አስምቷል ሰብኳል ። (የሐዋ. ሥራ 8 ፡ 26—40) የቤተክርስቲያን ታሪክ አባት የሚባለው አውሳብዮስ “ጃንደረባው (ኀፅው) ለወገኖቹ ሐዋርያ ሆነ” ሲል መስክሮለታል ። ( Eu. church History 11, 1. 13) ተመልከት ። ከሐዋርያትም መካከል ኢትዮጵያ ገብተው እንዳስተማሩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈዋል ። ቅዱስ ማቴዎስ ማስተማሩን ሩፊኖስና ሶቅራጥስ ፥ ቅዱስ እንድርያስ እንዳስተማረ ጀሮም (ኢየሮኒሞስ) ቅዱስ ቶማስ እንዳስተማረ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በታሪክ ቤተክርስቲያን አረጋግጠዋል ።
(Rufinus Eecl, hist, x, G and socrates I19, Cat. script 1.262 Hom 31)ተመልከት

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ክርስትናን ብትቀበልም ፤ በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶስ መንበር የተሰጣት ሶርያዊው ፍሬምናጦስ ከኢትዮጵያ ተልኮ በ330 ዓ.ም. ጵጵስናን ከእስክንድርያ ከመንበረ ማርቆስ ከቅዱስ አትናቴዎስ እጅ ተቀብሎ በመጣ ጊዜ በ4ኛው ምዕተ ዓመት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከዕርዕ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መልሷል ፤ በትምህርተ ወንጌል መላይቱን ኢትዮጵያን ስላበራት አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በሚል የሙገሳ ስም ይጠራል ።

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪት በሕገ ወንጌል እምነቷ በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ የተመሰረተች መሆኗን በዚህች አጭር ታሪካዊ ዘገባ ለማመልከት ተሞክሯል ፥ የምትከተለውም የሃይማኖት ቀኖና ከጉባኤ ኬልቄዶን በፊት የነበሩትን የኒቅያን የቁስጥንጥንያንና የኤፌሶንን የሃይማኖት ውሣኔዎች ነው ። በዚህ ምክንያት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ትባላለች ። ሌሎች መጤ ባሕሎች ሳይቀላቀሉባት ከሌሎች አስቀድማ ከእግዚአብሔር ጋር የተዋወቀች ሀገረ እግዚአብሔር መሆኗ የትንቢቱን እውነተኛነት ያረጋግጥልናል ።

ለዓምደ ሃይማኖት ትምህርታችን መግቢያ በመጠኑ የሃይማኖቱን የትመጣነት ካሳየን ዘንድ ወደ ዋናው ሐሳባችን ገብተን ለሃይማኖተ ወንጌል



www.ethiopianorthodox.org

ለክርስትናችን ምስክር የሚሆኑትን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቀኖና (Biblical Canon) ዝርዝር አነዝና ወደ ኢትዮጵያችን ቋንቋ በየጊዜው ወደ ግዕዝ ልሣን እየተተረጎሙ እንዴት እንደመጡና ለምን ስ ቤተክርስቲያናችን እንደምትቀበላቸው ሐተታ ብንሰጥ እንወዳለን ።

"ቅዱሳት መጻሕፍት" የሚባሉት ብሉያትና ሐዲሳት ናቸው ቁጥራቸውም በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ተጠቅሷል ። ". . .በእንተ ኍልቈ መጻሕፍት አምላካውያት ዘእዙዝ ተወክፎቶን ኀበ ቤተክርስቲያን ቅድስት ዘኍልቆሙ 80 ወ1ዱ" ይላል ሁለተኛው አንቀጽ ምእመናን በጉባኤ ሊቀበሏቸው የታዘዘ ቁጥራቸው ሰማንያ አንድ የሚሆን አምላክ አገዛዞ ያጻፋቸው የአምላክን ነገር የሚናገሩ የመጻሕፍትን ቁጥር ይናገራል ። ሲል በአርእስቱ መጀመሪያ ላይ ይገልጻል ። እሊህም መጻሕፍት ብሉያቱ 46 ፣ ሐዲሳቱ 35 ናቸው ። ሁሉም ተጠቃለው ቅዱሳት መጻሕፍት ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ተብለው ይጠራሉ ። ቅዱሳን ነቢያትና ሐዋርያት በተለያዩ ዘመናት በልዩ ልዩ ልሳናት (ቋንቋዎች) በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው የጻፏቸው ከሐሰትና ከኑፋቄ የተለዩ ሰውን ለንጽሕና ለቅድስና የሚያበቁ ክቡራት መጻሕፍት በመሆናቸው ብሉይም ሐዲስም በአንድነት ቅዱሳት መጻሕፍት በሚል ስያሜ ሊታወቁ ችለዋል ።

318ቱ ሊቃውንተ . . ቤተክርስቲያን በወሰኑት የሐዋርያት ሃይማኖት ማለትም በኒቂያው ጸሎተ ሃይማኖት ብሉያትና ሐዲሳት በጋራ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚባሉ ምስክር እናገኛለን ። "ወተንሥአ እምውታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት" ይላል ። ትርጉሙም "በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ" ሲል ይገኛል ። በብሉይም በሐዲስም ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ተጽፎአል ። ብሉይንና ሐዲስን ጸሎተ ሃይማኖታችን ቅዱሳት መጻሕፍት ብሎ ይጠራቸዋል ። ስለዚህም መጻሕፍቱ ቅዱሳን ይባላሉ ። ቅዱስ ጳውሎስም መጻሕፍቱን ቅዱስ መጽሐፍ እያለ ቅድስናቸውን ፣ በመንፈስ እግዚአብሔር መሪነት መጻፋቸውንና ለምን አገልግሎት እንደሚጠቅሙ ይገልጽልናል ። በ2ኛ ጢሞ. ምዕ. 3 በቁጥር 15—17 የተናገራቸውን ኃይለ ቃላት እንመልከት ።

"ቅዱስ መጽሐፍን ከሕጻንነትህ ጀምሮ ከማን እንደተማርክ ታውቃለህ! ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ሊያድንህ የሚችለውን በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ መጽሐፍ ሁሉ ለፍጹም ትምህርት ለተግሣጽ ለማስተማር በእውነት ለማራቀቅ ይጠቅማል ። የእግዚአብሔር ሰው በበጎ ምግባር ሁሉ ይመከር ዘንድ" ብሎ መጻሕፍቱ እንደ አንድ መጽሐፍ ተቆጥረው ብሉያቱና ሐዲሳቱም "ቅዱስ "ወይም" ቅዱሳት" በሚል ቅጽል ተሰይመው መጠራት እንዳለባቸው መስክሮልናል ። በሌላም ቦታ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ቅዱስ ጴጥሮስ ሐዋርያው ይመሰክራል ። እንዲህ ብሎ ። "ትንቢት ከሰው ፈቃድ ከሰውም ፍላጎት ከቶ አይሆንም ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ተናገሩ እንጂ ከእግዚአብሔር ተልከው" 2ኛ ጴጥ. ምዕ. 1:21 ከዚህ አነጋገሩም የተረዳነው ቁምነገር መጻሕፍቱን ቅዱሳት ያሰኛቸው መስፈርት ፣ መለኪያው በመንፈስ ቅዱስ የተቃኙ ቅዱሳን ሰዎች የጻፏቸው ስለሆነ "ቅዱሳት" በሚል ቅጽል መጠራት እንደሚገባቸው ነው ። (ግዕዝና አማርኛ የኦርቶዶክሱን ሐዲስ ኪዳን ተመልከት)

ሐዋርያት አከል ከሆኑት ከጥንታውያን ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ጽሑፎች ከድርሳኖቻቸው ስንመለከት ሐዋርያትን መስለው እንደ አበው ሐዋርያት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ቅድስናና እውነተኝነት ጠቀሜታም ያስረዱናል ። የታወቀው ስመጥር ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ይላል ። "ይደልወነ ናጽምዕ ቃላተ መለኮት ከመ ኢይባዕ ውስተ አልባቢነ ቃለ ነኪር" ።

—ባዕድ ቃል (ልብ ወለድ ፈጠራ) ወደ ልባችን እንዳይገባ ቃላተ መለኮትን ማድመጥ ይገባናል ። ሳዊሮስ ዘአስሙናይንም "መጻሕፍት አምላካውያት እስትንፋሰ አፉሁ ለእግዚአብሔር ነዮን ወዓዲ ይቤ እስመ መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉ ለእግዚአብሔር ፈጣሪ ወውእቱ ክቡር ወየዓቢ እምልብ ዘፍጡር . . ." መጻሕፍት አምላካውያት የእግዚአብሔር እስትንፋስ ናቸው። እንዲሁም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉን የፈጠረ የእግዚአብሔር ቃል ነውና እርሱም ክቡር ከፍጡር ሐሳብም ከፍ ያለ ነው ብሏል ቅዱስ ቄርሎስም በግጻዌ ድርሳኑ እንዲህ ይላል" ለትምህርተ ቅዱሳት መጻሕፍት ግሙራ አልቦ ዘይጸግቦ ወኢመኑሂ ወፈድፋደሰ እለ ይሔልዩ ጥበበ ወአጥረዩ እእምሮ ማሕየዌ ውስተ አልባቢሆሙ እስመ ጽሑፍ አኮ በኀብስት ዘየኀዩ ሰብእ አላ በኵሉ ነገር ዘይወፅእ እምአፉሁ ለእግዚአብሔር ሲሲተልብ ቃሉ ለእግዚአብሔር ውእቱ ወኀብስት መንፈሳዊ ዘያጸንዕ ኃይለሰብእ . . ."የቅዱሳት መጽሐፍትን ትምህርት ማናቸውም ቢሆን ከቶ የሚጠግበው የለም ። ይልቁንም ጥበብን ለሚሹና በልባቸው ማሕየዊ አእምሮን ለተገነዘቡ ፤ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በምትወጣ ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ እንዳይድን ተጽፎ አልና፣የልቡና ምግብ ሰውንም የሚያበረታ መንፈሳዊ ኅብስት የእግዚአብሔር ቃል ነው ።" ከዚህ በላይ ለምስክርነት የጠቀስናቸው የሊቃውንቱ አነጋገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ተገኝተው መጽሐፍ ቅዱሱን የሚተረጉሙ ናቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶቹን መመልከት ነው ። (የሐዋ. 19 ፣ 19 ዕብ.4 ፣ 12 ኤር. 23 ፣ 29 መዝ 118 97 - 94 ማቴ 4 ፣ 4 ሉቃ. 10 ፣ 42 ሉቃስ 11 ፣ 28 1ኛ ጢሞ. 4 ፣ 13 መጽሐፈ ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ ገጽ 48 ፣ 49)

የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች በኢትዮጵያችን ባሉት ታላላቆች ገዳማትና አድባራት በገጠር አብያተ ክርስቲያናት እንኳን ሳይቀሩ የቅዱሳት መጻሕፍት የብራናው በቁም ጽሕፈት በእጅ የተጻፉት ተበታትነው እንጂ እንደ ማሕተሙ መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ላይ ተጠርዘው አለመገኘታቸው የታወቀ ነው ። አራቱ ወንጌሎች ለየብቻ ተበታትነውና አንድ ጥራዝ ሳይሆኑ ባሉበት የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍል ሆነው ይታመናሉ ። የኦሪትም የነቢያትም የሐዋርያት መልእክታትም እንደዚሁ ለየብቻ በአንድ ጥራዝ ሳይታወቁ በመጽሐፍ ቅዱስነታቸው ይታወቃሉ በማሕተም ያሉት እንኳን ለየብቻ የሚሆኑበት ጊዜ አለ ሐዲስ ኪዳን ለብቻው ብሉይ ኪዳን ለብቻው ታትሞ ይገኛል ከሐዲስም ከብሉይም ለየብቻ ተነጣጥለው የታተሙም ብዙዎች ናቸው ። የመጽሐፍቱም ለየብቻቸው ታትመው መገኘት ማለት መጻሕፍቱ በጥራዝ ስላልተገናኙ መጽሐፍ ቅዱስነታቸው ተሽሮ ከቀኖና መጽሐፍ ቅዱስነት (ከሕጋዊነት) ያወጣቸዋል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው ።

አንዳንድ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ቁጥር በጥራዝ አንድ መሆንና አለመሆን እንደሚወስነው በማሰብ በዝርዝር ያሉት 66 ወይም 65ቱ ብቻ ሕጋዊ (ቀኖናዊ) እንደሆኑና ከዚያ ውጭ ያሉት ግን በሐዋርያት ሲኖዶስና በሰለስቱ ምዕት ቀኖና የታወቁትን ሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት ፣ ሌሎች የእምነት ዘርፎች የማይቀበሏቸው እንደ ብሉይና ሐዲስ ኪዳን አፖክሪፋ (Apocrypha) በማድረግ ይቆጥሯቸዋል ። በነገራችን ላይ አፖክሪፋ ማለት አይሁዶች አንቀበላቸውም ያሏቸው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ጭምር የሚያጠቃልል በተለይም ከኦርቶዶክስ ውጭ ባሉ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው መጻሕፍት ናቸው ። በተለይም በጣም የሚገርመው መጽሐፍ ቅዱስ ከልደተ ክርስቶስም በፊት ሆነ በኋላ ባሉት ቅዱሳን በተለያዩ ዘመናት መጻፋቸን ዘንግተው በነቢያትና በሐዋርያት ዘመን በአንድ ጥራዝ የተጠረዘ ይመስል ወይም ከዚያን በኋላ ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከዘመነ ሊቃውንት እስከ ዘመናዊ የማተሚያ መኪና መፈልሰፍ ድረስ ቅዱሳት መጻሕፍት ተበታትነው ያሉ እንጂ በጥራዝ አንድ አለመሆናቸው እየታወቀ ፣ በጥራዝ ካሉት 66ቱ መጻሕፍት ውጭ

> — ከኋላ ቀርነት የሚከፋው በሥልጣኔ ሰበብ የሰውን የአእምሮ ሕሊናዊ ሚዛን የሚያቃውስ ልቅ ነፃነት ነው ።



መለከች

www.ethiopianorthodox.org

እንቀበልም የብሉይና ሐዲስ አፖክራፋ ናቸው ማለታቸውን ስናጤነው ነው በጥን ታዊቱ ቤተክርስቲያን ታሪክ በሐዋርያትና በሊቃውንት ትውፊት ግን ተበታትነው በአንድ ጥራዝ ያልሆኑት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ባሉበት ለምስክርነት ይጠቀሳሉ ቀኖናዊነታቸው (ሕጋዊነታቸው) የታመነ ሆኖ ሲጠቀሱ ሲተረጉሙ ኑረዋል ።

ይህ ታሪክ በኋላ ለተነሱት ተቃዋ ሚዎች እንግዳ ሆኖ ለመቀበል ቢያዳግ ታቸውም በኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የታወቁና ሕጋዊነታቸው የታመነ ነው ። ተቃዋሚዎቹ ዘወትር እንደመረጃ አድርገው ከ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጥራዝ ውጭ ያሉትን በቤተክርስ ቲያናችን ተቀባይነት ያላቸውን መጽሐፍት ቀኖናዊነት እንደሌላቸው በማድረግ የሚያቀርቧቸው የተለመዱ ጥቅሶች ከኦ ሪት ዘዳግም ምዕ. 4 ቁ. 2ና ከራእየ ዮሐንስ ደግሞ ምዕ. 22 ቁ. 18ን ነው ጥቅ ሶቹን ግን ብንመረምራቸው የቅዱሳት መጻሕፍትን ቁጥር ሲወስኑ አናገኛቸ ውም ። በኦሪት ዘዳግም የተጻፈው ሙሴ ከእግዚአብሔር አግኝቶ በጻፋቸው ትእዛ ዞች ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ ተገቢ እንዳልሆነ ያመለክታል ። እንጂ የመጻ ሕፍቱን ቁጥር አይወስንም ። ምናልባት በአስተያየት ከሔድን ሙሴ ከጻፋቸው ፭ቱ ብሔረ ኦሪት መካከል በኦሪት ዘዳግም የተጠቀሰው ኃይለ ቃል ኦሪት ዘፍጥ ረትን ዘፀአትን ዘሌዋውያንና ዘኁ ልቊን ይመለከት ይሆናል ። ሌሎቹን የብሉይ መጻሕፍት ይመለከታል እንዳንል ከሙሴ ዕረፍት በኋላ በዘመነ መሳፍንት በዘመነ ነገሥት በዘመነ ካህናት የተጻፉ ስላሉ እነዚያን ሁሉ ለአንዱ የተነገ ረው አጠቃለለ ማለት አይቻልም ። ቢባልም በፀሐፊዎቹ መካከል የዘመን መራራቅ ስላለ አይሆንም በራእየ ዮሐን ስም የተጠቀሰው ሐተታው አስተያየቱ እንደ ኦሪት ዘዳግም ነው ። መጨመር አይ ቻልም ብሎ በቁጥር 18 የተጠቀሰውም ሆነ ማጉደል አይገባም ብሎ በቁጥር 19 የተወሳው በራእየ ዮሐንስም ላይ መጨመ ርም መቀነስም የሚያስቀጣ መሆኑን ከማመልከት አልፎ አይናገርም ።

ከዚህም ውጭ ስለብሉያትም ሆነ ሐዲሳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቁጥር ቀኖና አይወስንም። ዮሐንስ ራእይ የተጻፈውም ከሐዲሳት እንኳን በዘመን እንደማይገኝም ታውቋል ። ከላይ እንዳስረዳነው መጽሐፍ ቅዱስ እንደዛሬው 66በአንድ ጥራዝ በሙሴና በቅ/ዮሐንስ ወንጌላዊ ዘመን ነበር ለማለት የማይቻል ነው ። በአንድ ጥራዝም ተሰ በሰቡ ፣ ተበታትነውም ለየብቻም ተጠረዙ በቅዱሳት መጻፍት ቀኖና ላይ የሚያ መጣው ተጽዕኖ አለመኖሩን ማወቅ ይገባል (ኵክሐ ሃይማኖት ከገጽ 278 ገጽ 281 ተመልከት)

የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥራቸው 81 ነው ብለናል ። በዝርዝር እነማን ናቸው ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ መስጠት አስፈላጊና ተገቢም በመሆኑ ከዚህ በታች በዝርዝር እናቀርባለን ።

ሀ. የብሉያት መጻሕፍት 46 ናቸው ።
ለ. የሐዲሳት መጻሕፍት 35 ናቸው
በድምሩ 81

## የ46 ብሉያት ዝርዝራቸው

| | |
|---|---|
| 1/ ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደት)<br>2/ " ዘጸአት<br>3/ " ዘሌዋውያን<br>4/ " ዘኁልቁ<br>5/ " ዘዳግም | አምስቱ ብሔረ ኦሪት (5ቱ የሙሴ መጻሕፍት ይባላሉ ።) |
| 6/ መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ<br>7/ " መሣፍንት<br>8/ " ሩት | ከ1-8 ያሉት 8ቱ ብሔረ ኦሪት ይባላሉ (ከ5ቱ መጻሕፍተ ሙሴ ጋር ተደምረው ሲቆጠሩ ነው ።) |
| 9/ መጽሐፈ ዮዲት | |
| 10/ 1ኛ መጽሐፈ ነገሥት (ቀዳማዊ ሳሙኤል) | መጻሕፍተ ሳሙኤል ነቢይ እንደ አንድ ተቆጥረዋል ። (በሳሙኤል ተጀምረው በነቢዩ ጋድና ናታን ተፈጽመዋል) |
| 11/ 2ኛ መጽሐፈ ነገሥት (ሣልስ ራብዕ ነገሥት) | መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ እንደ አንድ ተቆ ጥረዋል ። "ወለዳግማዊ ነገሥት ጸሐፍያ ናታን ወጋድ" ይላል ናታ ንና ጋድ ጽፈውታል በየጊዜው የተነሡ ነቢያትም ፈጽመውታል |
| 12/ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ<br>13. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ (አራተኛ ምናልባ ዘዜና መዋዕል የሚ ቆጠር) | በፍትሐ ነገሥት ሁለቱን መጻሕ ፍት ሕፁፃን ይላቸዋል ። መጻሕፈ ድርያሚን ወይም ተረፈ ነገሥት ይባላሉ ፣ አቀማመጣቸው በቤተ ክህ ነትና በቤተ መንግሥት እንደ ነበረ ይተረጓል ። |
| 14. መጽሐፈ ዕዝራ ፣ (ዕዝራና ነህምያ) | ነህምያ በግዕዙ ብሉይ ኪዳን ከዕ ዝራ ጋር የሚቆጠር የዕዝራ ተከ ታይ ነው ። |
| 15. ሱቱኤል ዕዝራ ፣ ካልዕ ዕዝራ ፣ | እንደ አንድ ይቆጠራል። ዕዝራ የዳግማ ወዱ ባቢሎን ምርኮና የሚጠት (ከምርኮ መልስ) ሁለት መጽሐፍ በመጻፉ ፣ |
| 16/ መጽሐፈ አስቴር ፣ | መጽሐፈ አስቴር ካልዕ የተባለው መጽሐፍ ከአስቴር የተከፈለ የዚያው ዘርፍ ስለሆነ በአንድነት ይቆ ጠራል |
| 17/ መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ ፣ | (መቃቢስ ዘአልዓዛር መቃቢስ ዘሞ ዓብ የጻፉት እንደ አንድ ተቆጥሮ ዋል ። በመስጴጦሚያና በግብጽ ያለው አንድ ወገን ተቆጥሮ ማለት ነው ።) |
| 19/ መጽሐፈ መቃብያን ዳግማዊ ፣ | (መቃቢስ ዘብንያም የጻፈው ነው ። በሞዓባዊያንና በሚዶናውያን ያለው እንደ አንድ ተቆጥሮዋል ።) |



www.ethiopianorthodox.org

20/ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ፤
21/ መጽሐፍ ኢዮብ
22/ መዝሙረ ዳዊት ፤
23/ መጽሐፈ ምሳሌ ዘሰሎሞን ፤

(የመጻሕፍተ መቃብያን ሁለተኛ ክፍል)

24/ መጽሐፈ ተግሣጽ (ቆሐልት) ፣

(በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተጣምሮ ይቆጠራል ። በግዕዙ ግን ተከፍሎ ነው)

25/ መጽሐፈ ጥበብ ፤
26/ መጽሐፈ መከብብ(ጥበበ ባንር) ፤

(ባጎር የሰሎሞን የፍልርፍና ስሙ ነው ። )

27/ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ፤

(ምሳሌ ተግሣጽ ጥበብ መክብብና መኃልይ ፣ 5ቱ የሰሎሞን መጻሕፍት ይባላሉ ።)

28/ ትንቢተ ኢሳይያስ ፤
29/ ትንቢተ ኤርምያስ ፤

(ባሮክ ፣ ሰቆቃው ፣ ተረፈ ባርክ ) ከኤርምያስ የወጡ ስለሆነ ከኤርምያስ ጋር ይቆጠራሉ ። ለየብቻቸው ሳይሆን በአንድነት ማለት ነው።

30/ ትንቢተ ሕዝቅኤል ፤
31/ ትንቢተ ዳንኤል ፤

(ስብሐተ) ጸሎተ 3ቱ ደቂቅ ፣ ታሪክ ሶስና ቤል ከይሲ ከዳንኤል የወጡ ስለሆነ ከዳንኤል ጋር አንድ ሆነው ይቆጠራሉ ።
(ኢሳይያስ ፣ ኤርምያስ ፣ ሕዝቅኤልና ዳንኤል እሊህ 4ቱ በፍትሐ ነገሥት ዓበይት ነቢያት ፤ (ታላላቅ ነቢያት) ይባላሉ ። ዐበይትነታቸው በዕድሜ ሳይሆን በዕውቀት በማዕረግና በድርሰት ብዛት ነው ።)

32/ ትንቢተ ሆሴዕ ፤
33/ ትንቢተ አሞጽ ፤
34/ ትንቢተ ሚክያስ ፣
35/ ትንቢተ ኢዩኤል ፤
36/ ትንቢተ አብድዩ ፤
37/ ትንቢተ ዮናስ ፤
38/ ትንቢተ ናሆም ፤
39/ ትንቢተ ዕንባቆም ፤
40/ ትንቢተ ሶፎንያስ ፤
41/ ትንቢተ ሐጌ
42/ ትንቢተ ዘካርያስ
43/ ትንቢተ ሚልክያስ

(ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ የተጠቀሱት 12ቱ ነቢያት ንዑሳን ወይም ደቂቀ ነቢያት ይባላሉ ። ንዑስነታቸውም በዕድሜ ሳይሆን በዕውቀት በማዕረግ በድርሰት ማነስ ነው ።)

44/ ጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክ (መጽሐፈ ሲራክ)
45/ መጽሐፈ ኩፋሌ ፣

(ከአራት የተከፈለ የዘመናትን ቁጥርና የመላእክትን ተፈጥሮዋቸውን የሚናገር መጽሐፍ ነው ።)

46/ መጽሐፈ ሄኖክ ፤

(ከመጽሐፍት ሁሉ በፊት በነቢዩ በሄኖክ ከማረጉ በፊት የተጻፈ ከጥንታዊው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ወደ ግዕዝ የተተረጐመ ሐዋርያው ይሁዳ ምዕ. 1 ቁጥር 14—15 ለምስክርነት የጠቀሰው መጽሐፍ ነው ። የዕብራይስጡ የብራና ጥቅልል ቁንጽሉ በሙት ባሕር በተደረገው የአርኪኦሎጂ ምርመራ ተገኝቶ ከግዕዝ ጋር አንድ ሆኖ ተገኝቷል ። ለዚህም በእነ ዶክተር ጌታቸው ኃይሌ የቀረበውን ጥናት መመልከት ይጠቅማል ።)

ወደ ገጽ 22 ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ለ/ የ35ቱ ሐዲሳት ዝርዝራቸው

ከገጽ 6 የዞረ

1/ የማቴዎስ ወንጌል
2/ የማርቆስ ወንጌል
3/ የሉቃስ ወንጌል
4/ የዮሐንስ ወንጌል

4ቱን ወንጌሎች የጻፉ ሁለቱ ከ12ቱ ሐዋርያት ፤ ሁለቱ ከ72 አርድእት ናቸው ። ስለ አጻጻፋቸው ታሪክ አሞንዮስ አውሳብዮስ በተባሉት ሊቃውንት ተጽፎ በመቅድመ ወንጌል ይገኛል ።
በማቴዎስ ወንጌልና በሉቃስ ወንጌል ስለ ክርስቶስ ልደት ከአበው ተጀምሮ ሲቆጠር እስከ ዮሴፍ ስለተጻፈ የዘር ሐረጉን (Genealogy) ከድንግል ማርያም ጋር ለማያያዝ የነገረ ማርያም መጽሐፍ ለወንጌል መርገፍ ሆኖ እንደሚያገለግል ማስተዋል ይገባል ።

5/ የሐዋርያት ሥራ (ግብረ ሐዋርያት)
6/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች፣
7/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
8/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
9/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ገላትያ ሰዎች ፤
10/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ቆላስይስ ሰዎች ፤
13/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16. የጳውሎስ መልዕክት ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17/ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ቲቶ
18/ ,, ,, ,, ወደ ፊልሞና
19/ ,, ,, ,, ወደ ዕብራውያን

ከቁጥር 6—19 ያሉት 14ቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክታት ይባላሉ ።

20/ የጴጥሮስ መልዕክት 1ኛ
21/ ,, ,, 2ኛ
22/ የዮሐንስ መልዕክት 1ኛ
23/ የዮሐንስ መልዕክት 2ኛ
24/ የዮሐንስ መልዕክት 3ኛ
25/ የያዕቆብ መልዕክት
26/ የይሁዳ መልዕክት

ከቁጥር 20 እስከ ቁጥር 26 የተዘረዘሩት መጻሕፍት (7ቱ የሐዋርያት መልዕክታት) ይባላሉ ።

27/ የዮሐንስ ራዕይ

(አቡቀለምሲስ ተብሎም ይጠራል)

28/ ሥርዓተ ጽዮን - ሲኖዶስ
29/ ትዕዛዝ - ረስጠአ
30/ ግጽው-ረስጠብ
31/ አብጥሊስ-ረስጠጅ

ከቁጥር 28—31 ያሉት 4 ክፍል ሲኖዶስ ይባላሉ ። የጻፉአቸውም ሐዋርያት ናቸው ። ቅዱስ ጳውሎስም ተሳትፎበታል ።
ኩክሐ ሐይማኖት ገፅ 113 ተመልከት ጌታ ከሞት ከተነሳ በኋላ 40 ቀን እስከ ዕርገት ለሐዋርያት ያስተማራቸው ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ነው ። (ግብ.ሐዋ ምዕ. 1ቁ.3) ተመልከት ።

32/ 1ኛ መጽሐፈ ኪዳን
33/ 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን

34/ ቀሌምንጦስ

(3ቱ የቀሌምንጦስ መጻሕፍት እንደ አንድ ተቆጥረዋል ። ቀሌምንጦስ የቅዱስ ጴጥሮስ ረድእ ነው ። ከቅ/ጴጥሮስ አግኝቶ ጽፎታል ። በ90 ዓ/ም ገደማ የሮማ ሊቀ ጳጳስ ሆኗል ።)

35/ ዲድስቅልያ

(የቤተክርስቲያንን ሥርዓትና ትምህርት የያዘ መጽሐፍ ነው ። ሐዋርያት ፤ ቅዱስ ጳውሎስም ጭምር 4ቱን ሲኖዶስ ሲወስኑ ዲድስቅልያንም ጽፈዋል ።)

ለዛሬው የ81ዱን መጻሕፍት ዝርዝርና ታሪካዊ አመጣጥ ለማሳየት ተሞክሯል ። በሚቀጥለው እትማችን ትርጓሜያቸውን እናቀርብለን ።

www.ethiopianorthodox.org